Australian Government

COVID-19 VACCINATION

# ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት ስለመዘጋጀት

ወቅታዊ የሆነበት ቀን: 30 ሐምሌ/July 2021 ዓ.ም

## የርስዎ ዝርዝር መረጃ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ

የርስዎ ቀጠሮ እስኪደርስ ሲጠብቁ ለመዘጋጀት ማድረግ የሚችሉት አንዳንድ ነገሮች አሉ።

የሚፈቀድልዎት ከሆነ ለርስዎ መዲኬር ወቅታዊ ወቅታዊ/ up to date with Medicare, ዝርዝር መረጃ እርግጠኛ ስለመሆን ማረጋገጥ (መዲኬር የማይፈቀድልዎት ከሆነም ለኮቪድ/COVID-19 ክትባት ማግኘት ይችላሉ)። ይህንን ማድረግ የሚችሉት:

- መዲኬር አካውን ኦንላይን አካውንት/Medicare online account በ myGov በኩል
- በ Express Plus Medicare app።
- ለ Medicare program በመደወል።

ለርስዎ የተቀናጀ አካውንት ከሌለዎት ማድረግ የሚችሉት:

- Enrol in Medicare, እስካሁን ካልተመዘገቡ።
- Set up በመዲኬር ላይ ተመዝግበው ከሆነ ለርስዎ መዲኬር በኦንላይን መስመር ላይ ማቀናጀት፤ ነገር ግን መዲኬር ከሌለዎት ወደ myGov. ማገናኘት።
- Get an Individual Health Identifier (IHI), ለመዲኬር የማይፈቀድልዎት ከሆነ።

የርስዎን ክትባት ከወሰዱ በኋላ ለክትባት መውሰድ ማረጋገጫ የሚሆን የበሽታ መከላከያ ክትባት መግለጫ ጽሁፍ ወረቀት ማግኘት ይችላሉ። ይህንን how to get your immunisation history statement በአገልግሎቶች አውስትራሊያ ድረገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።

## ለርስዎ ቀጠሮ ዝግጁ መሆን

በአውስትራሊያ እና በሞላው ዓለም የተወሰነ ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች አቅርቦት እንዳለ ነው። ይህ ማለት በኮቪድ/ COVID-19 ከፍተኛ ችግር ላለባቸው እና/ወይም በቫይረሱ መጋለጥ ለሚችሉት ሰዎች ክትባቱን በቅድሚያ ያገኛሉ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ በየጊዜው ክትባቱን ያገኛሉ። በቅድሚያ ክትባት ማግኘት እንዳለበት መረጃ በድረገጽ www.health.gov.au/covid19-vaccines ላይ ገብቶ ማየት። በድረገጽ https://covid-vaccine.healthdirect.gov.au/ ላይ ገብቶ በማየት ለኮቪድ/ COVID-19 ክትባት ቀጠሮ ማቀናጀት ከቻሉ ለማጣራት ይችላሉ።

በኮቪድ/COVID-19 ክትባት መስጫ ቀጠሮ ላይ መገኘት **የለብዎት** እርስዎ:

- ደህና ካልሆኑ ማለት ከኮቪድ/COVID-19 ጋር በተዛመደ ትኩሳት፤ ጉንፋን፤ በአፍንጫ ፈሳሽ ወይም ሌላ የበሽታ ምልክቶች ካለብዎት
- ለኮቪድ/COVID-19 የምርመራ ውጤት እየተጠባበቁ ከሆነ
- በምርመራ ውጤት የኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ ከተገኘብዎት እና ከሰው ተገልለው ከሆነ
- በተገለሎ ማቆያ ላይ ከሆኑ
- ከኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ ካለበት የሆነ ሰው በቅርበት ግንኙነት አድርገው ከሆነ ነው።

ከዚህ በላይ ካሉት በማንኛውም ላይ ከወደቁ ከበሽታ መከላከያ አቅራቢዎ ጋር ማጣራት። ክትባት ለመውሰድ ያለዎትን ቀጠሮ እንደገና ማቀናጀት ይኖርብዎት ይሆናል። ኮቪድ/COVID-19 ክትባቶች ለኮቪድ/COVID-19 ህክምና በጥሩ ላይሰሩ ይችላሉ።

ካለዎት የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ቀጠሮ በፊት በ 7 ቀናት ውስጥ ሌላ ክትባት ወስደው ከነበረ ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ መናገር አለብዎት። የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ እንደገና ያለዎትን ቀጠሮ እንዲቀይሩት ሊጠይቅዎት ይችላል።

ክትባቱን ከመውሰድዎ በፊት ትኩሳት ወይም የሆነ ትንፋሽ በሽታ ምልክት ከሌለብዎት ለኮቪድ/COVID-19 ምርመራ ማካሄድ አያስፈልግዎትም።

## ለሁለት ጊዜ መጠኖች/doses ቀደም ብሎ እቅድ ማውጣት

የሁለት ጊዜ መጠን/ doses ለርስዎ ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ማግኘቱ ጠቃሚ ነው። ቢያንስ በሶስት ሳምንታት ልዩነት መካከል ሁለቱንም መጠን/dose የኮቪድ/COVID-19 Pfizer [Comirnaty] ክትባት ከወሰዱ፤ የ AstraZeneca ኪቪድ/COVID-19 ክትባትን ካገኙ በሁለት ጊዜ መጠን አወሳሰድ መካከል የ12 ሳምንታት ልዩነት መኖር አለበት። በመጠን/dose ክትባቶች መስጫ መካከል ያለውን የጊዜ ገደብ ከ12 ሳምንታት ወደ 4 ሳምንታት ዝቅ ማድረጉ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ትክክለኛ ሊሆን ይችላል። የሁለተኛ መጠን/dose ከወሰዱ በኋላ እስከ አንድና ሁለት ሳምንት ጊዜ ከኮቪድ/COVID-19 ቫይረስ ሙሉ በሙሉ መከላከያ አይፈጠርም።

## በርስዎ የክትባት መስጫ ቀጠሮ ላይ ምን እንደሚጠበቅ

በርስዎ ኮቪድ/ COVID-19 ክትባት መስጫ ቀጠሮ ላይ የሚከተሉትን ማምጣት አለብዎት:

- ካለዎት ፎቶ ያለው መታወቂያ/ID
- ካለዎት መዲኬር ካርድ
- ባለዎት ሥራ ምክንያት የኮቪድ/COVID-19 ክትባት የሚሰጥዎት ከሆነ ለተቀጣሪ መታወቂያ/ID።
- ስላለዎት የህክምና ሁኔታዎች፤ አለርጂ፤ የደም መዛባት ወይም የበሽታ መቋቋም ሀይል አቅም መዳከም/immunocompromise (ይህ የመቋቋም ሀይል አሰራር መዳከም) መረጃ ይሆናል
- እየወሰዱ ላሉት ማንኛውም መድሃኒቶች መረጃ
- ቀደም ሲል ለተሰጥዎት ማንኛውም ኮቪድ/COVID-19 ክትባት (የክትባት ምልክት ዓይነት እና ክትባት የተሰጠበት ቀን) መረጃ
- ባለፈው ጊዜ ለወሰዱት ስለ ማንኛውም ክትባቶች መረጃ
- በአሁን ጊዜ ላለዎት አጠቃላይ ሀኪም/GP/s እና ለሚያዩት ልዩ ባለሙያ ሀኪሞች ስም
- የፊት መሸፈኛ ጭንምብል (በርስዎ አስተዳደር ግዛት/ተሪቶርይ አስፈላጊ ከሆነ) መያዝ።

በርስዎ ቀጠሮ ጊዜ በርስዎ የበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢ ስለሚሰጥዎት ኮቪድ/COVID-19 ክትባት ማንኛውንም ጥያቄ አቅርቦ መወያየት ይቻላል።

እድሜዎት ከ60 ዓመት በታች ከሆነ፤ ማንኛውም የጤና ሁኔታዎች ካለብዎት ወይም የሆነ መድሃኒት የሚወስዱ ከሆነ ለበሽታ መከላከያ ክትባት አቅራቢዎ መናገር። በተለይ ለእነሱ መናገር ያለብዎት፤ እርስዎ:

- ቀደም ሲል ከተሰጠ ኮቪድ/COVID-19 ክትባት መጠን/ ወይም በክትባት ንጥረ ነገር ላይ አለመስማማት አለርጂክ ፈጥሮብዎት ከሆነ
- በሌላ ክትባቶች ወይም ሌላ መድሃኒቶች ላይ የአናፍይላክሲስ/anaphylaxis (ከፍተኛ የሆነ የአለርጂ ዓይነት ችግር) ከነበረብዎት
- ቀደም ሲል ኮቪድ/COVID-19 መጠን/ dose ክትባት በኤክስፐርት ክትትል ግምገማ የተገኘ ሌላ ከባድ አንጻራዊ ሁኔታ ተፈጥሮ ከነበር
- ህክምና የሚያስፈልገው ከማስቶችይቶሲስ/ mastocytosis ጋር የተያያዘ አለመስማማት/anaphylaxis የታወቀ ታሪክ ካለብዎት
- ለካፒላርይ ማንጠብጠብ ችግር በምርመራ ከተገኘብዎት
- ከትሮምቦችይቶፐኒያ/thrombocytopenia ጋር የተገናኘ ከፍተኛ የቨነስ/venous እና/ወይም የአርተሪያ ትሮምቦሲስ/arterial thrombosis ችግር ከነበረብዎት፤ በዚህ ቀደም ሲል የኮቪድ/COVID-19 መጠን ክትባትን ከወሰዱ በኋላ በምርመራ የትሮምቦቲክ ትሮምቦስይቶፐኒች ዝግመት ችግር(TTS) መገኘትን ያካትታል
- የሰረብራል ቨኑስ ሳይነስ ትሮሞሲስ/cerebral venous sinus thrombosis (HIT)፤ የሀፓሪን ማነቃቂያ ትሮምቦችይቶፐና/ heparin induced thrombocytopenia (CVST)፤ በሆድ እቃ ቨንስ ላይ የደም መርጋት (splanchnic veins) ወይም ከደም መርጋት ጋር የተያያዘ አንቲፎስፎሊፒድ ዝግመት ችግር/ antiphospholipid syndrome ካለብዎት
- የማዮካርዲቲስ/myocarditis እና/ወይም ፐሪቻርዲቲስ/pericarditis ከነበረዎት

- አሁን ወይም በቅርቡ ጊዜ የማይድን የቁርጥማት ህመም/rheumatic fever ወይም ኢንዶካርዲቲስ/endocarditis አለብዎትን
- በተፈጥሮ የልብ በሽታ ካለ
- የልብ ካርዲኦምዮፓትይ/cardiomyopathy ምስፋት (እድሚያቸው ከ 30 ዓመት በታች ለሆኑ)
- ከባድ የልብ ሥራ ማቆም
- የሌላ ሰው ልብ አግብተው ከሆነ
- የመድማት ችግር ካለብዎት ወይም ደም እንዳይረጋ ማድረጊያ ህክምና (የደም ማቅጠኛ) መድሃኒት የሚወስዱ ከሆነ
- እርጉዝ ከሆኑ
- ያለዎት የበሽታ መቋቋም ሀይል/immunocompromised (ይህ ማለት የበሽታ መቋቋም ሀይም አሰራር ደካማ መሆን ወይም የበሽታ መቋቋም ሀይምን የሚያዳክም መድሃኒት የሚወስዱ ከሆነ)
- ቀደም ሲል የኮቪድ/ COVID-19 ቫይረስ ከነበረብዎት፤ ወይም በኮቪድ/COVID-19 ቀጣይ የሆነ ህመም ካለብዎት
- ሌላ አዲስ (በትኛው አዲስ በወጣ) የኮቪድ/COVID-19 ክትባት ከወሰዱ
- ባለፉት 7 ቀናት ውስጥ የሆነ ዓይነት ክትባት ወስደው ከነበር ነው

በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ለክትባት ቀጠሮ ከማቀናጀትዎ በፊት ከርስዎ ጤና እንክብካቢ አቅራቢ ጋር ስለ ክትባት መውሰድ መነጋገሩ የተሻለ ሊሆን ይችላል። እንዲሁም በሚወስዱት *ክትባት ስላለው ለየት ያለ መረጃ* ማንበብ ይችላሉ:

- *መረጃ ስለ ኮቪድ/COVID-19 Pfizer (Comirnaty) ክትባት፤* ወይም
- *መረጃ ስለ AstraZeneca ኮቪድ/COVID-19 ክትባት*

## ክትባቱን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ

ክትባቱን በመርፌ ተደርጎ፤ በአብዛኛው በላይኛው ክንድዎ ጅማት ላይ ይሰጥወታል። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ ቢያንስ ለ15 ደቂቃዎች የሚሆን ለመከታተል በክትባት መስጫ ክሊንክ ውስጥ መቆየት አለብዎት። ባለዎት የጤና ታሪክ ተመርኩዞ በክሊኒኩ ውስጥ ለ30 ደቂቃዎች እንዲቆዩ ሊጠየቁ ይችላሉ።

## በርስዎ ቀጠሮ ላይ ያቀረቡት መረጃ እንዴት እንደሚጠቅም

የርስዎ ግላዊ ዝርዝር መረጃ እንዴት እንደሚወሰድ፤ እንደሚቀመጥ እና እንደሚጠቅም መረጃ ለማግኘት በድረገጽ: https://www.health.gov.au/using-our-websits/privacy/privacy-notice-for-covid-19-vaccinations ላይ ማየት።